# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

## ዓለም-አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናከብር፣

**(ዛሬም ለዴሞክራሲና ፍትህ የሚደረገው ትግል ያለሴቶች ንቁ ተሣትፎ ግቡን አይመታም እንላለን!)**

ከኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የተሰጠ መግለጫ

የካቲት ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ. ም
March 5, 2010

በኢትዮጵያ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስኮች እንደ ወንዶች ሁሉ የሴቶችም ተሳትፎ ጉልህና አንጸባራቂ ለመሆኑ የትናንቱም፣ የዛሬውም ታሪካችን በቂና ጉልህ ምስክር ነው። በተረጋጉ ጊዜያት ብቻ ሳይሆን በቀውጢ ወቅቶችም ጭምር ኢትዮጵያውያን እህቶቻችን የመፍትሄ ቋት መሆን ብቻ ሳይሆን ለሃገር ነጻነት፤ ለወገን እኩልነትና ለፍትህ በተደረጉ ተከታታይና ቀጣይ ተጋድሎዎች የግንባር ሥጋ በመሆን ክቡር ገድልን አስመዝግበውና መስዋዕትነቶችን ከፍለው የብቁ ዜግነት ተምሣሌቶች ለመሆን ችለዋል፤ እስከዛሬም ይኸው አርዓያነታቸው እንደቀጠለ ነው።

የኢትዮጵያ ሴቶች የትግል ታሪክ ጥንተ-አመጣጥ እጅግ ረጅምና ውስብስብ ቢሆንም በተለይ ሃገራቸው በጠላት እጅ በወደቀችበት በአምስቱ የጣልያን ወረራ ዓመታት ከወንድሞቻቸው ጎን ተሰልፈው ፈታኙን ዘመን በጀግንነት ለመወጣት በማስቻል ረገድ የተጫወቱት ልዩ ሚና በኢትዮጵያ የነጻነት ትግል ታሪክ ማህደር ውስጥ ክቡር ሥፍራ ይዞ ይኖራል፡፡

የአገዛዝ ሥርዓቱ ከሰማየ ሰማያት የመጣና በሥዩመ-እግዚአብሄር የተወሰነ አድርጎ በሃሰት እየሰበከና እያጭበረበረ የኢትዮጵያን ሕዝብ ግማሽ ምዕተ-ዓመት ያህል ለመግዛት በበቃው የፊውዳሉ ሥርዓት ወቅት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ይደርስባቸው የነበረውን ድርብርብ ጭቆና ለማስወገድ በብርቱ ታግለዋል። በትምህርት መስክ ወደፊት እንዳይራመዱ፣ በልዩ ልዩ ዘመናዊ የኢኮኖሚ መስኮች በብዛት እንዳይሳተፉና በቤት ውስጥ ሥራ ብቻ ተወስነው እንዲቀሩ ይገፋፋ የነበረውን የወቅቱን ሥርዓት ሁዋላ-ቀር ፖሊሲዎች

**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Siver Spring , MD 20910**

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 301-578-4466** **Fax: 301-449-8363** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

አጥብቀው ታግለዋል። በማናቸውም መስክ ከወንዶች እኩዮቻቸው እኩል መሆናቸውን በተግባር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቀጣይ ትግሎችንም ሲያደርጉ ቆይተዋል። በኋላም የየካቲት ስልሳ ስድስቱ ሕዝባዊ አብዮት የኢትዮጵያ ሴቶች ይደርሱባቸው ከነበሩ ተደራራቢ ጭቆናዎች ይላቀቁ ዘንድ ልዩ አጋጣሚን ፈጥሮላቸዋል።

ድህረ-የካቲት ስልሳ ስድስት የኢትዮጵያ ሴቶች ግንባር ቀደም መፈክራቸው የነበረውን “ድርብ ጭቆና ይውደም!” በማንገብ፤  በጾታ፣ በሙያና በሌሎችም ልዩ ልዩ መስኮች ይደርሱባቸው ከነበሩ ጭቆናዎች ለመገላገል ከወንዶች ወንድሞቻቸው ጋር ያበሩበት ልዩ ወቅት ነበር። በዚህም ወቅት ነበር ኢሕአፓ የሴቶችን ጥያቄ የዋነኛው የፀረ-ፊውዳል ትግሉ አካል መሆኑን በማስተማርና ያለሴቶች ተሳትፎም ሕዝባዊው ትግል ግቡን እንደማይመታ በመቀስቀስ ጉልህና ታሪካዊ የሆነ ሚና የተጫወተው። ሴቶች እህቶቻችን መብታቸውን በተግባር ማስከበር የሚችሉት ተደራጅቶ በመታገል መሆኑን በማስረገጥ በሠራተኛና ሕዝባዊ ማኅበራት እንዲሁም በዘመኑ በተፈጠሩ ዴሞክራሲያዊ ግንባሮች ውስጥ ጉልህ ሚና እንዲኖራቸውም ኢሕአፓ ሳያሰልስ አንቅቷል፤ አደራጅቷል፤ በግምባር ቀደምትነት ታግሎ አታግሏል። በዚህም ምክንያት በወቅቱ የሴቶች ማኅበራት ቁጥር እንዲበራከት ማስቻል ብቻ ሳይሆን የጾታ አቻዎቻቸው አባል በሆኑባቸው ሌሎች የሙያና ሕዝባዊ ማኅበራት ውስጥ ሴቶች ከተራ አባልነት እስከ አመራር ደረጃ በብቃት ሊያገለግሉ የሚችሉባቸውን አጋጣሚዎች በመፍጠር ረገድ ኢሕአፓ ወቅታዊ ሕዝባዊ ግዴታውን ተወጥቷል።

በድህረ-የካቲት ስልሳ ስድስት ወቅቶች በሴቶች ጥያቄ ዙሪያና በጠቅላላው የወቅቱ ፀረ-ፊውዳል ትግል ሂደት ውስጥ በአርዓያነታቸው ዘላለማዊ ለመሆን ከበቁት ውስጥ እነማርታን፣ ዳሮ ነጋሽን፣ ሰላማዊትን፣ መዝገብነሽን፣ አጥናፍነሽን፣ ጌራን፣ ድላይን፣ ጀሚላንና ሌሎችንም አያሌ ቆራጥ ታጋይ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን በዚህ አጋጣሚ ማስታወሱ አግባብነት አለው፤ በየዓመቱ የሚከበረው ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን የነዚያን ቆራጥ ታጋዮች ገድል ሳንገድፍ እንድናነሳና ተገቢውን ክብርም እንድንሰጣቸው ያስገድደናል። የጥቂት ምርጥ መኮንኖች ስብስብ የነበረው ወታደራዊው ደርግ የቀለበሰውን ሕዝባዊ አብዮት ላለማስነጠቅ በአሻፈረኝ-ባይነት ሲታገሉ በየእሥር ቤቱና በየፈፋው ለጋ ህይወታቸው የተቀጠፈውን በሺህ የሚቆጠሩትን የወቅቱን የሕዝባዊው ትግል አርበኞች ከቶም ልንዘነጋቸው አይገባም።

የኢትዮጵያ ሴቶች ከላይ በአጠቃላይ በጠቀስነው መልክ ለረጅም ዓመታት የፍትህና የእኩልነት መከበር ጥያቄን መፈክሮች አንግበውና ትግላቸውን በከፍተኛ መስዋዕትነት አጅበው እንደቀጠሉ ቢሆንም ዛሬም ድረስ ጭቆናው መልኩን እየቀያየረ ከመከሰት አልተገታም። በአሁኑም ወቅት  የኢትዮጵያ ሴቶች ተቀጥረው በሚያገለግሉባቸው የሥራ መስኮች ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያን መነፈጋቸው አልቀረም። በቤት ውስጥ አስተዳደር መስክ ሃላፊነቱ በአብዛኛው ከነሱ ጫንቃ ላይ አልወረደም። ለወሊድ ቁጥጥርና ከወሊድ

ጋር ለተያያዙ ጤና ነክ ጉዳዮች በቂ እንክብካቤና ድጋፍ አይደረግላቸውም። በተለይም በገጠር የሚኖሩቱ በበቂ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ዕጦት ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶች ዋነኛ ተጠቂዎች ናቸው። በአመዛኙ የሥራ ዕጦት ባስከተለው ችግርም ላለው መንግሥት ገቢ በሚያመጡ ደላሎች አማካይነት ብዙ ሺህ እህቶቻችን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች እየተጋዙ ከባርነት ባልተለየ መልክ የዐረብ ከበርቴዎች አገልጋይነት ተዳርገዋል። በሚደርስባቸው ግፍ ብዛት ራሣቸውን ለማጥፋት የሚገደዱ እህቶቻችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። ይህን የዘንድሮውን ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን ስናከብር በነዚህ እህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን ግፍ በማሰብና በከፍተኛ ቁጭትም ነው።

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ውስጥ በተለይ በፖለቲካው መስክ ለሴቶች መደራጀትም ሆነ ንቁ ተሣትፎ ልዩ ድጋፎችና ማበረታቻዎች በጉልህ አይታዩም። በትግሉ ቆርጠው ህይወታቸውን ጭምር ለመስጠት የደፈሩቱ ዛሬም እንደትናንቱ ለአምባገነን አገዛዞች ጥይት ወይም ለእሥር ቤት ይዳረጋሉ። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በጠመንጃ ለሥልጣን የበቃው ጎጠኛውና አሸባሪው የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት እንደ ቀድሞዎቹ የአፄውና የአምባገነኑ የደርግ አገዛዞች ሁሉ በሴቶች እህቶቻችን ላይ ለሚወርደው ግፍና አበሳ ምንም ደንታ የለውም። ከላይ የጠቀስናቸው በዐረብ አገሮች እየተንገላቱ ያሉት እህቶቻችንን ከሚያስገቡት የውጭ ምንዛሬ ከመጠቀም አልፎ እየደረሰባቸው ያለውን በደል ለዓለም መንግሥታት አቤት በማለትም ይሁን የያገሩን መንግሥታት በቀጥታ በመገናኘት ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግ አንዳችም ግልጽ ርምጃ ሲወስድ እንኳ አይታይም። ይልቁንም ለሌሎች እህቶቻቸው አርዓያ ለመሆን የበቁ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ሴቶች ታጋዮችን ማፈን፣ ማሰር፣ ደብዛቸውን ማጥፋትና መግደልን የሰርክ ተግባሩ አድርጎታል። ጀግናዋ የኢሕአፓ ታጋይ አበራሽ በርታን ከሌሎች የትግል ጓዶቿ ጋር ደብዛዋ እንዲጠፋ አድርጓል። የአንድነት ድርጅት ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በፈጠራ ክስ ወህኒ ወርውሮ በማሰቃየት ላይ ይገኛል።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ብዙ ሺህ ሕፃናት ከድሆች እህቶቻችን እየተነጠቁና በገንዘብ እየተደለሉ፣ ለምዕራብ አገሮች በማደጎ ስም በገፍ እየተሸጡ በዓመት $100 ሚልዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ስለሚያመጡለት ገዢው ቡድን በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚያደርሰው በደል ለልጆቻቸው፤ ለልጅ ልጆቻቸውና ለቀጣዩ ትውልድ ተረካቢ ጭምር እንዲተርፍ በማድረግ ላይ ነው። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል ዛሬም እንደከርሞው የጠቅላላው ሕዝባዊ ትግል አካል ነውና ያለማቋረጥ በአምባገነኖች የሚደርስበትን በትር እየመከተ ለድል ወደሚያበቃው ወደ ዋናው የትግሉ ግብ ወደ ዴሞክራሲያዊትና ፍትሃዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ ከመትመም አልተገታም፤ ሊገታም አይችልም።

ስለዚህም ዘንድሮም ዓለማቀፍ የሴቶችን ቀን የምናከብረው ለትግሉ የተሰውትን ሁሉ በማሰብና ወደማይሸራረፈው ግባችን ማለትም ወደ ሕዝባዊት-ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ ለምናደርገው ትግል ቃል ኪዳናችንን በማደስ ሊሆን ይገባል፤ ነውም። ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ዛሬም እንደትናንቱ ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ የሚደረገው

ሕዝባዊ ትግል በሴቶች ተሣትፎ መታገዝ እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ለዚህም ተግባራዊነት እገዛና ድጋፍ ከማድረግ ከቶውንም ወደኋላ አይልም፤ ከምሥረታው ጀምሮ ለቆመለት ዓላማና በሂደት ላስመዘገበው አኩሪ ታሪክ ዘለዓማዊነት ከወገኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም በቆራጥነትና በግምባር ቀደምትነት ትግሉን ይቀጥላል።

**ያለሴቶች ተሣትፎ ሕዝባዊው ትግል ግቡን አይመታም!**
**የሴቶች እኩልነት በተግባር ይረጋገጣል!**
**እናቸንፋለን!**